ጤናማ የክርስቲያን እድገት

በሲንክሌር ቢ. ፈርጉሰን

ዘ ባነር ኦፍ ትሩዝ ትረስት

Copyright © **The Banner of Truth Trust 1991**
Originally published in English under the title Healthy Christian Growth
By the Banner of Truth Trust, Edinburgh EH12 6EL,UK
All rights reserved.

Translated and printed by MERF-ET Team

+251911790701

ክርስቲያን ማለት በክርስቶስ አዲስን ሕይወት የጀመረ ማለት ነዉ።መንፈሳዊ ሕይወት ጤናማ በሆነ መንገድ ማደግ አለበት። ክርስቲያን ማለት አዲስ እንደ ተወለደና ማደግ የሚፈልግ ሕጻን ማለት ነዉ (1ጴጥ 2፡2)

ጤናማ ልጅ ለማደግ የሚያስፈልት ነገሮች ምግብ፣ፍቅር እንክብካቤ ሲሆን ጡንቻዎቹ እንዲያድጉ ደግሞ እንቅስቃሴ ይህን ከበሽታ እንዲጠበቁ ያደርጋል። ብዙዎቻችን ይህን ለማደግ እነዚህን ያገኘን ሲሆን አንዳንዶች ግን ይህን በበቂ ሁኔታ ስላላገኙ በሕይወት ዘመናቸዉ ሁሉ በልጅነታቸዉ ያጡትን ነገር አሁን ለማግኘትና ለማካካስ ሲታገሉ እናያለን።ክርስቲያንም እንዲሁ በተመሳሳይ መልኩ በልጅነት ጊዜያችን ጤናማ አስተዳደግ ካላደግን ስናድግ ክርስቲያናዊ ብስለት ይጎድለናል። ዉጤቱም ክርስቲያናዊ እድገት ላይ ያልተመጣጠነ ሕይወት ይኖረናል ማለት ነዉ። ይህ ጸሁፍ የሚገልጸዉ ‹‹ እግዚአብሔር ነገሮች እንዲያደጉ እንደሚፈልግ የሚያስረዳ ነዉ›› (1ቆሮ 3፡7)። በክርስቲያናዊ ሕይወት ለማደግ ከመፈለጋችን በፊት መጠየቅ ያለብን መሰረታዊ ጥቂዎች አሉ።ወዴት ነዉ ማደግ ያለብኝ? መጨረሻዉስ ምንድን ነዉ? የሕይወቱ ትርጉም ምንድን ነዉ? እንዲህ አይነት ጥያቂዎች ከምዕተ አመታት በፊት በእምነት አባቶች ዘንድ ይጠየቅ ነበር መልሱም ደግሞ ‹‹ የሰዉ የመጨረሻዉ ግቡ እግዚአብሔርን ማክበርና በእርሱ መደሰት ነዉ››

እንዴት ነዉ ለእግዚአብሔር ክብርን የምናመጣዉ? አጭሩ መልስ ክርስቶስን እየመሰልን ስናድግ ነዉ።ከአራቱ ልጆቻችን ዉስጥ አንዱ ጥርሱን ታሞ ወደ አንድ የጥርስ ሐኪም ዘንድ ሄዶ ሲያማክር ሐኪሙም አራቱም ጥርሶች መወገድ አለበት ብሎ መለሰለት። ጥርሶቹ በትክክለኛዉ ስፍራ ላለመቀመጣቸዉ ለእኛ የሚነግረን ነገር ምንድን ነዉ? ትንሽዋን ፍርሃት ከጥርስ ሐኪሙ ጋር አነጻጽር ነገር ግን በልጃችን አፍ ዉስጥ ሌላ ጥርሶች የሚበቅሉበት ስፍራ እስካሁንም ድረስ ይኖራል። ሚስቱ የጥርስ ሐኪሙ የሆነዉን ነገር በቤተሰባችን ዉስጥ ስትናገርና ልጁ አራቱን ጥርስ እንደሚያጣ ሲያስብ ፊት በጣም ተጨማደደ ከዚያም እንዲህ በማለት አረጋገጠ ‹‹ ችግር የለም ፊታችንን እናሳድጋለን››

ይህ እንደ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ነገር በእኛ ላይ የሆነ ነዉ። እኛ ክርስቶስን በመምሰል ማደግ አለብን ሰዎች እኛ ክርስቲያኖችን ሲያዩ ክርስቶስን ሊያዩት ይገባል። የእኛ ሕይወት የክርስቶስ ሕይወት ነዉ። ጳዉሎስ እንደተናገረዉ እስክንበስል ድረስ ማደግ አለብን *‹‹...የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ...›› (ኤፌ 4፡13)* ‹‹...ነገር ግን

እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ (ኤፌ4፡15)፤ የእግዚአብሔር ዓላማ ‹‹...አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና (ሮሜ 8፡29)

የክርስቲያን ብስለቱ ክርስቶስን መምሰሉ ነዉ የክርስቲያን እድገት ወደ ‹‹ፊታችን ማደግ ነዉ›› በክርስቶስ ፊት ሰንቆይ ወይም ስንመገብ እርሱን ወደ መምሰል እንለወጣለን(2ቆሮ 3፡18)

ነገር ግን ይህ እንዴት ይሆናል?

በስጋ ሕይወት ማደግ የሚወሰነዉ መመገብ፣እንቅስቃሴ፣ለማደግ ምቹ የሆነ ሁኔታ መኖር የግድ ነዉ፤ በክርስትናም እንዲሁ ለማደግ ልምምድና እንቅስቃሴ ማድረግ ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገትና ብስለትን ያመጣል፤

መመገብ

‹‹የምንመገበዉን ምግብ ምን እንደምንመስል ያሳያል›› ያለዉ ፈላስፋዉ ሲሆን ሰዎች ሲያዩን በተፈጥሮ ካገኘነዉ ማንነት ጋር ያገናኙናል፤እንደ ሌሎቹ የስህተት ትምህርቶች ሁሉ በንግግሩ ዉስጥ ትንሽ እዉነትን እናገኛለን፤ለዚህ ነዉ ተመሳሳይ ቋንቋ የተጠቀምነዉ የምንመገበዉ ምግብ ማንነታችን ይገልጻል ስለዚህ ጉዳይ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፤

ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።...የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤...ሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል(ዮሐ 6፡27፣35፣51)

የእዉነተኛ ክርስቲያን እድገት የሚወሰነዉ በክርስቶስ የሚመገበዉ ምግብ ነዉ፤

ስምኦን ጴጥሮስ ይህ ትምህርት በደንብ ስለገባዉ አንባቢዎቹን እንዲህ በማለት ያሳስባል *‹‹ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆኑ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ›› 1ጴጥ 2:2-3*

ይህ ንጹህ የሆነዉ መንፈሳዊ ወተት ምንድን ነዉ? የጴጥሮስ መልእክት ያለጥርጥር እዉነተኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነዉ፤(1ጴጥርስ 2፡22፣23፣24)፤ እኛ የምንፈልገዉ ወተት

የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስን ነዉ፤መመኘት ይኖርብናል፤ አዲስ የተወለደ ሕጻን ምን እንደሚፈልግ ታስታዉሳላችሁ፣ ሲርበዉ ያለቅሳል የሚፈልገዉን ምግብ መስጠት ጴጥሮስም የሚለን ነገር ቢኖር እንደዚህ ሕጻን ተመኙ ነዉ የእግዚአብሔርን ቃል አስተምህሮ መፈለግ ይሁዳም በተመሳሳይ ቁ.20 ላይ *‹‹እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ››* ይህን እንዴት መፈጸም እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል

የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።(2ጢሞ 3፡16-17)

ክርስቲያን ለአገልግሎት በቃሉ አስተምሮ መያዝ አለበት ጳዉሎስ እዚህ ጋ የሚናገረዉ በወንጌል ዉስጥ ከተጠቀሰዉ ጋር ተመሳሳይ ቃል ሲሆን ይህም ደቀመዛሙርት አሳ ለማጥመድ መረባቸዉን እያጠቡ፣ እያስተካከሉና እየተዘጋጁ ካለዉ ቃል ጋር ይመሳሰላል፤ በአራት መንገድ ለክርስቶስ አገልግሎት ዝግጁነት አለዉ፤

በማስተማር

በተፈጥሮ አእምሮአችን ጨለማና በሐጢአት የተበከለ ነዉ(ሮሜ1፡21፣25)፤ አሁን ግን ክርስቲያኖች የምናስበዉን ነገር ሁሉ በትክክል ማወቅና በአምሳሉ የፈጠረንን ጌታ መምሰል ይኖርብናል (ዘፍ 1፡27)

እግዚአብሔርን የሚያዉቁ ሰዎች ይበረታሉ (ዳን11፡32) እግዚአብሔርንና ባህርይዉን ልናዉቅ ይገባል፤ ከዚያም የእኛን ፈቃድ፣እኛነታችንን እና ሀጢአታችንን ማየት ይኖርብናል፤ ስለክርስቶስና ስለ ጸጋዉ ስለ እምነት ጉዞና ስለ መጪዉ አለም ማወቅ አለብን፤እኛ ልናዉቅ የሚገባዉን ነገር ጌታ ይገልጥልናል፤በመጽሐፍ ቅዱስ ዉሥጥ ነዉን አይደለም ጴጥሮስ ያለዉ እንደ ሕጻን ልጅ የቃሉን አስተምህሮ ስንመኘዉና ስንፈልገዉ ነዉ፤ ይህን ትዕዛዝ የሚተካዉ ነገር የለም፤ የማናጠናዉ ከሆነ ወድቀናል ማለት ነዉ፤

በመግሰጽ

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ወደ አእምሮአችን ደርሷል ነገር ግን በዚህ ማቆም የለበትም፤ለህሊናችን መናገር አለበት ወደ ስህተት ጎዳና ስንሄድ ያሳየናል፤

ብዙ ሰዎች ራሳቸዉን ማየትና መገምገም አይፈልጉም ስህተት ሲፈጽሙም ራሳቸዉን አይተዉ ማስተካከል አይፈልጉም፤ ነገር ግን በክርስትና ሕይወታችን እያደግን ስንሄድ ራሳችንን የምናታልልበት ያልተወሰነ ችሎታ አለን፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በመንገዳችን ላይ ያስቆመናል፤ ይህን ለማድረግ የሚጠቀመዉ መጽሐፍ ቅዱስን ነዉ፤ ዳዊትን በነብዩ ናታን በኩል እግዚአብሔር ሲናገረዉ እናነባለን፤ በመጀመሪያ እንደ አንባቢም እንደ አድማጭም ዳዊት በሀጢአት እንደወደቀ እናያለን፤ ከዚያም ሐይለኛ የሆነ ድምጽ እንሰማለን መንፈስ ቅዱስም ወደ እኛ እያመለከተ እንዲህ ይለናል ‹‹ ለአንተ ነዉ የምናገረዉ›› (2ሳሙ 12፡7) እግዚአብሔር በመንገዳችን ላይ ተናግሮ ይመልሰናል፤

ልምምዱ ከባድ ቢሆንም ጤናማ የሆነ ነዉ በስህተት ጎዳና የምንሄድ ከሆነ ወደ ግባችን ልንደረስ አንችልም፤ ስለዚህ በስህተት ጎዳና እየሄድን ‹‹ ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነዉ›› ማለት አንችልም (መዝ 119፡105)

ማስተካከል

የእንግሊዝኛዉ (ኮሬክቲንግ) የሚለዉ ትክክለኛዉ ቃል ሳይሆን ትክክለኛዉ ትርጉም ግን ጳዉሎስ ያለዉ ‹‹መታደስ›› ነዉ፤ የግሪኩ ቃል ኦሮቶዶንቲክ ማለት (ያልተስተካከሉ ጥርሶችን ማስተካከል) ማለት ነዉ፤ ከፈዉስ ጋር የተያያዘ ቃል ነዉ፤ጳዉሎሰ እንዳለዉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መልእክት የሰዎችን ሕይወት የመፈወስ፤የማደስና የመጠገን ሐይል አለዉ፤ ይህም ቅንጅታዊ የሆነ የክርስቲያን ዕድገት ነዉ፤ የክርስቲያን ህብረት የሚያስፈልገዉ ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸዉ እንዲጽናኑና እንዲበረቱ በእግዚአብሔር ቃል እንዲጠነክሩ ማድረግ ነዉ፤

በጽድቅ ላለዉ ምክር

የእግዚአብሔር ቃል ሕጻን ልጅ እንደነበርን ጊዜ ወተት መጠጣት ብቻ ሳይሆን ሕይወታችን እንዲጠነክር ወደ ስፖርት ትምህርት ቤት ገብተን እንደሚለማመድ ሰዉ አይነት

ያደርጋል፤አጥኑት፣ተረዱት፣ታመኑት መንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንዲጠነክር ለጸጋዉ ቃል ምላሽ መስጠት ይገባል፤ ለጌታ አላማ መኖር እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ አስተሳሰብ መኖር ይገባል፤

በምትመራዋ የእግዚአብሔር እጅ መመራትና እንደሚያስፈልግ ባሪያ ፈንጋይ የነበረዉ በኋላም መዝሙር ጸሐፊዉ ዮሐንስ ኒዉተን በደንብ ያዉቀዋል፤

እርሱም ሲጠይቅ እንዴት ነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንጠብቀዉ?... በአጠቃላይ እርሱ ሕዝቡን ይመራል፣ ይመግባል፣ጸሎትን ይመልሳል፣ የመንፈስ ቅዱስን ብርሃን ይሰጣል ይህም መጽሐፍ ቅዱስን እንድንረዳዉና እንድንወደዉ የሚያደርግ ነዉ፤ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሎተሪ እጣ መጠቀም ወይም ትንሽዋን ነጥብ ወይም አንድን ክፍል ብቻ በማንበብ መመራት የለብንም፤ነገር ግን በድንጋጌ ይመራናል፣ ባህሪያችንን የሚመራ ተጽዕኖ የሚፈጥር ነዉ፤

ፍሬያማ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት ጠቃሚና ደስተኛ የሆነ ሕይወት ለመኖር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፤እነዚህም አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች ስላሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አብሮ መኖር ያስፈልጋል፤ ይዘቱም መንፈሳዊ ወተት ስለሆነ ይህን ወተት ለመጠጣት መፈለግ አለብን፤ መጽሐፉን ለማጥናት ፈቃደኛ ካልሆንን መንፈሳዊ እርጅና ዉስጥ ነዉ የምንሆነዉ፤ ልጅነት ደስ ይላል እንዳናድግና ተመጣጣኝ ምግብ እንዳንመገብ የሚከለክለዉን በሽታ ማስወገድ ነዉ፤

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ትራባለህ? እዉነተኛ ክርስቲያን ይራበዋል፤

መለማመድ

ልምምድ ልብን ያጠነክራል አለበለዚያ ግን እድገታችን ደካማ ይሆናል፤ አንድ ታዋቂ የሩሲያ ዘፋኝ እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር‹‹ ለአንድ ቀን ልምምዴን ባቆም ልዩነቱን አየዋለሁ ለሁለት ቀን ልምምዴን ባቆም ካምፓኒዉ ያዉቀዋል ለብዙ ቀናት ባቆም እድምተኝኛዉ ልዩነቱን በደንብ ያዉቀዋል፤››

ያለልምምድ በአንድ ጊዜ ወደ እድገት ጫፍ ላይ መድረስ አይቻልም ስሜት፣ፍጥነት፣ጸጋ እና ሰዓት ያስፈልጋል፤ጤናማ የሆነ መንፈስ በጥቂት ጊዜ ዉስጥ ሊያድግ አይችልም፤ያረጁ ክርስቲያኖች ስለ መንፈሳዊ ልምምድ ይናገራሉ ይህም ጥሩ የሆነ አገላለጽ ነዉ፤

ነገር ግን የእኛ መንፈሳዊ ልምምድ ምንድን ነዉ?

አምልኮ

በሕይወትህ ውስጥ እጅግ በጣም አስፈላጊዉ ጉዳይ እግዚአብሔርን ማምለክ ነዉ። የተፈጠርንበት ዋና አላማ ይህ ሲሆን በሁሉም ነገር ጌታን ማመስገን ነዉ። መዝሙረኛዉ ዳዊት ሲናገር ‹‹ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን።›› መዝ 103፡1።በትልቅ ደረጃ ላይ የደረሰዉን መንፈሳዊ ሯጭ የሚያሳይ ነዉ። በሁለንተናዊ ሕይወት በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን ማምለክ ነዉ።

ሕይወታችን በሙሉ ለጌታ ልንሰጥ ይገባል።እርሱን ማመስገንም ይገባል (ሮሜ 12፡1-2) በእግዚአብሔር ሐይል ላይ በሁለንተናችን ትኩረት ስናደርግ በመዝሙርና በጸሎት እናመሰግነዋለን። ለዚህም ነዉ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሰርተህ ሰባተኛዉን የእረፍት ጊዜ ያደረገዉ (ዘፍ2፡2-3 ዘጸ 20፡8-11፣ ኢሳ 58፡13-14) በዚያን ጊዜ በጋራ በመሰባሰብ እና አብሮ በማምለክ አንደኛዉ ሌለኛዉን በማነጽ እርስ በርስ ይማማራሉ ማለት ነዉ (ቆላ3፡16)

ክርስቲያኖች እያደጉ ሲሄዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴት ያለዉ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዉም በወንጌላዉያን አምልኮ ላይ ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት። በተቃራኒዉ ደግሞ የዘመኑ ስብከት ግን አጭር ሰዓት(ከአስር ደቂቃ ያልበለጠ) ነገር ግን ቃሉ የማይለዉን የሚሉ የሚወስድ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት ማለት ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሆነ ነዉ። እርሱን ማምለክና ከእርሱ ጋር ሕብረት ማድረግ ነዉ። (ዮሐ10፡3-4፣14)። በዚህ ጊዜ 30 ደቂቃ የስብከት ጊዜ አጭር ሊሆን ይችላል። በክርስቲያን ሕብረት ዉስጥ ይህ ትልቅ ትርጉም ያለዉ ነዉ። ስብከቱ መጽሐፍ ቀዱሳዊ ካልሆነ እና ጌታ የሚፈልገዉ አይነት ካልሆነ ግን (2ጢሞ 3፡16-4፡2) በቃሉ እዉነት ማደግ ያስፈልገናል።

2) ዕዉቀት

ክርስቲያን ማለት የዘላለም ሕይወት ያለዉ ነዉ (1ዮሐ5፡11) ይህ ማለት እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅን ያጠቃልላል።(ዮሐ 17፡3) ይህ ዕዉቀት ግላዊ ሲሆን ለእኛ አስፈላጊዉ ጉዳይ ‹‹በጸጋ ማደግ፣በጌታችንና በአዳኛችን ዕዉቀት መደግ አስፈላጊ ነዉ።(2ጴጥ 3፡18)።ጳዉሎስ እንዳለዉ በዕዉቀት ማደግ አስፈላጊ ነዉ በጸሎቱ ሁልጊዜ የሚያሳስበዉ እና ሸክሙ ‹‹*የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ*

ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤›› ኤፌ 1፡17-19 ፊሊ. 1፡19 ቆላ 1፡9)››

ይህ በዕውቀት ማደግ የሚከናወነው እንዴት ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማርነውን እና የተረዳነውን ነገር ስንተገብረው ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት፣ማወቅና መረዳት የእኛ ማዕከላዊ እንቅስቃሴ መሆን አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል የምንማርበት በቤተክርስቲያን ወይም በሌላ ስፍራ ይኖራልን? በማጥናት ብቻ ነው መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማወቅ የሚቻለው የእርሱን ባህርይና መንገድም የምናውቀው በማጥናት ነው። በክርስትና ሕይወታችን ለማደግ ከፈለግን ስርዓት ባለው መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ነው።

ከዚህ በታች መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደምናጠና ምክር አዘል መልእክት አቀርባለሁ። በስፋትና በጥልቀት አንብቡ።

በስፋት ማንበብ፡- **ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ላታውቁ ትችላላችሁ ስለዚህም ይህን ለማወቅ በስፋት ማንበብ ያስፈልጋል። ቁጭ ብላችሁ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍን አንብቡ።ወደ መኝታ ቤት ስትሄዱም በማለዳም አንብቡ ከዘፍጥረት ጀምራችሁ አንብቡ።ለምሳ ሳንደዊች በልታችሁ ከሆነ በሌላ ጊዜ ደግሞ የጳውሎስን መልእክት ለሁለት ሳምንት በተከታታይ አንብቡ።በሚቀጥለው ሳምንታት ደግሞ ሌሎች መልዕክቶችን አንብቡ። ከወንጌላት ውስጥ አንዱን እሁድ ከሰዓት ለወር ያህል አንብቡ።የሐዋርያት ስራንና ራዕይን ቅዳሜ ከሰዓት አንብቡ። የሚጠቅማችሁም ከሆነ ከወዳጆቻችሁ ጋር አንብቡ። የምትደማመጡ ከሆነ አንደኛው ድምጹን ከፍ አድርጎ ያንብብ ሌላው ይስማ። በወር ውስጥ አዲስ ኪዳንን አንብባችሁ ትጨርሳላችሁ። እንደዚሁ ብሉይ ኪዳንን አንብባችሁ መጨረስ ትችላላችሁ ይህም ጥቂት ትጋትና ራስን ማስገዛትን ይጠይቃል።በስፋት በማንበብ ብዙ የሚያስደንቅ ነገር ትማራላችሁ።**

በጥልቀት ማንበብ፡- **እንደ ልጅ የተደነቅሁት (የአያቶቹ ትውልድ) በመጨረሻው ዘመን ምን እንደሚመስል ሲናገሩ ስመለከት ረጅሙን ጊዜ ማሰብና ማሰላሰል የመብሰል ምልክት ነው። ማሰብ፣ማሰላሰልና፣ማኘክና መዋጥ ለእኔ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።የሚያድጉ ክርስቲያኖች በትዕግስት መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑና የሚያሰላስሉ ናቸው።መጽሐፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው።(2ጢሞ 3፡16) ስለዚህም ይህ መገለጥ ስለሆነ በልባችን የመጀመሪያውን ስፍራ የያዘ ሊሆን ይገባል።ይህም ጠቃሚ ሀሳብ ነው።ለምሳሌ የጥሞና ጊዜ**

ወስደህ በወራትና በሳምንታት በመከፋፈል ዘፍጥረትንና ዘጸአትን፣ ማረቆስንና ዮሐንስን፣ መዝሙረ ዳዊትንና መጽሐፈ ምሳሌን፣ የሐዋርያት ስራንና ሮሜን ማጥናት ያስፈልጋል፤ከአንዳንድ አስተማሪዎችና ጥሩና ሊታመኑ የሚችሉ የማብራሪያ መጽሐፍቶችን ማንበብ ጠቃሚ ነዉ መጸጸት የለብህም፤

ብዙ ጠቃሚ የሆኑ መጻሕፍት በምታዉቁአቸዉ ሰዎች ተጽፈዉ ይሆናል ድንቅ የሆነዉን የክርስቶስን ፍቅር ለመረዳት ቅዱሳን በአንድ ላይ በመሆን እርስ በርስ በመተናነጽ ማደግ ያስፈልጋል(ኤፌ 3፡18፣4፡15-16) ዛሬ ብዙ በመጻሕት ቤት ያሉትን መጻሕፍት የሚመታና ክርስትናን የሚያኮስሱ መጽሐፍቶች አሉ፤ እንደ አቴንስ ሰዎች በሰዉ ብልሃት የተፈጠረዉን ፍልስፍና መጽሐፍ ከማንበብ ይልቅ ክርስቲያናዊ መጽሐፍትን ማንበብ ለእኛ እጅግ ጠቃሚ ይሆናል(ሐዋ 17፡21)፤ እናንተ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ናችሁ፤ ደቀመዝሙር ማለት *ዲሳይፑለስ* ከሚለዉ የላቲን ቃል የመጣ ነዉ እርሱም ተማሪ ማለት ነዉ፤ እናንተ በክርስቶስ ትምህርት ቤት ዉስጥ ናችሁ ስለዚህ በደንብ አጥኑ፤

3) ምስክርነት እና አገልግሎት

ተፈጥሮአችን በሐጢአት የወደቅን ስለሆንን ራሳችንን ማዳን አለብን፤ነገር ግን ኢየሱስ የሞትን መንገድ አሳይቶናል ሕይወት አይደለም፤ *ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል(ሉቃ 9፡24)* በክርስትና ሕይወት ለማደግ(ለማግኘት) ሕይወትን ለጌታ አሳልፎ መስጠት ያስፈልጋል፤ ጳዉሎስ በጣም ጠንካራ የሆነ ነገር ሲናገር (ሞት በእኛ ይሰራል) አለ ከዚያም በሐይል ዉጤታማ ይሆናል (ሕይወት በአንተ ዉስጥ በሥራ ላይ ነዉ (2ቆሮ 4፡12)፤

ይህ በክርስቲያን ልብ ዉስጥ ይመሰክራል ስለ ክርስቶስ ለሌላዉ ሰዉ ለመመስከር ሰዎች እያፈሩ ነዉ፤ ልክ እንደ ጢሞቲዎስ አይነአፋር ስለነበር ጳዉሎስ ሲያበረታታዉ እንመለከታለን *‹‹እንግዲህ በጌታችን ምስክርነት ወይም በእስረኛው በእኔ አትፈር፥ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን ስለ ወንጌል አብረኸኝ መከራን ተቀበል፤›› 2ጢሞ1፡8፤* ስለ ክርስቶስ ለመመስከር ፍርሃትና ፍርክርክነትን አስወግደን ማደግ አለብን፤የወንጌል ሐሳብ ሊያበረታን ይገባል ምንያቱም ስለክርስቶስ ለሌላዉ መናገር ስለሚያስችለን ነዉ፤ በዚህ ጊዜ የመዳናችን ዋስትናም ይጨምራል፤ ለክርስቶስ ያለን መታዘዝ እና ደስታ ይጨምራል፤(ልጅ በነበርኩ ጊዜ የማደርጋቸዉን ነገር መርሳት አልችልም ስለ ክርስቶስ በጎዳና ላይ እየዘለልኩ

ለጓደኞቹ እመሰክር ነበር ምስክርነቱ ተቀባይነት ባያገኝም ክርስቶስ የገባዉ ኪዳን በረከት ይከተለናል የሚል ነዉ(ሉቃስ 10፡5-6)

ስለክርስቶስ በምንመሰክርበት ጊዜ ቃላቶቻችን የተጣሩ ላይሆን ይችላል በተለይ ሌሎችን ሰዎች ስናገለግል ማለት ነዉ የኢየሱስ ወደ እኛ ባሪያ ሆኖ በመምጣት እና ማገልገል ልብን የሚነካ ድርጊት ነዉ።(ማቴ 20፡28፣ፊሊ 2፡6-7) ልክ እንደ ጳዉሎስ እኛም የእርሱ ባሪያዎች ነን።(ሮሜ 1፡1) ስለዚህ ምክንያት እኛም ሌሎችን ለማገልገል ራሳችንን ባሪያ ልናደርግ ይገባል። እንዲህ ማለትን መማር አለብን‹‹ ራሳችንን አንሰብክም ነገር ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ነዉ (ምክንያቱም ኢየሱስ ጌታችን ነዉ እኛ ደግሞ የኢየሱስ ባሪዎች ነን።(2ቆሮ 4፡5)።ጳዉሎስ መናገር የፈለገዉ ክርስቲያኖች ክርስቶስን በመምሰል ማደግ እንደሚገባቸዉ ነዉ። ሌሎችን ስናገለግል የእርሱ መሆናችንን የምናሳይበትና ለእርሱ ያለንን ፍቅር የምንገልጽበት መንገድ ነዉ። ሌሎችን የማናገለግል ከሆነ ግን ክርስቶስን በመምሰል ማደግ አንችልም ክርስቶስን በመምሰል ካላደግን ደግሞ አላደግንም ማለት ነዉ።

ማገልገል ምን ነገሮችን የያዘ ነዉ? ለሌሎች ሰዎች መጸለይን፣ጊዜ መስጠትን፣ስጦታችንን መጠቀምን፣ ገንዘባችንን በማሰባሰብ ለክርስቶስ ስራ መጠቀምን አሁን ካለንበት ራስን ከመዉደድ ስርዓት በመዉጣት ክርስቶስን ማገልገል ፍጹም ነጻነት መሆኑን መረዳት። ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጹዕ ነዉ(ሐዋ 20፡35)

ለዚህ አይነቱ ልምምድ የተዘጋጀህ ነህን?

አካባቢ

እንክብካቤ፣ፍቅር፣ራስን አስገዝቶ በቤት መሆን ጥሩ ሕይወት ይጀምራል። በእኛ ማደግ ዉስጥ ወላጆቻችን፣ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ትልቅ የሆነ ስፍራ ያላቸዉ ሀብቶቻችን ናቸዉ። በመንፈሳዊ ነገር ሕጻን በነበርን ጊዜ ቤተክርስቲያን የማደጊያ ስፍራ ነዉ የአዲስ ኪዳን ቤተሰቦቻችን ናቸዉ። ኢየሱስ ራሱ ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር ‹‹የአባቴን ፈቃድ የሚያደርጉ እነዚህ ወንድሞቼና እና እህቶቼ ናቸዉ›› በማለት እንደቤተሰቦቹ ተመለከተ።(ማር3፡35)። ቤተክርስቲያን ማለት የአማኞች ቤተሰብ ናት(ገላ6፡10፣ኤፌ2፡19) የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናቸዉ። ስለ ወርቃማዉ መመሪያ ስለ የርስበረስ ፍቅር ሲናገር (ዮሐ 15፡12፣17፣ ሮሜ 13፡8፣ ኤፌ 5፡2፣1ተሰ4፡9፣ 1ጴጥ 1፡22፣1ዮሐ 3፡11-23፣4፡7-12)

በዚህ የፍቅር አካባቢ ውስጥ ምን ይፈጠራል? በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መንፈሳዊ እድገትና መበረታታት እንዴት ይሆናል? ክርስቶስ በሰጣቸዉ ጸጋ የሚያገለግሉ ለእኛ የተሰጡን ስጦታዎቻችን ናቸዉ።ብዙ የጸጋ ስጦታዎች ለቤተክርስቲያን የተሰጡ ሲሆን በእነዚህም ተጠቅመን እንድንበረታታ የሚመራን ናቸዉ(ሮሜ 12፡4-8፣ 1ቆሮ 12፡4-7፣ ኤፌ 4፡11፣ 1ጴጥ 4፡7-11) ሁሉም አላማቸዉ አንድ ነዉ ለማነጽ የተሰጡ ናቸዉ(ኤፌ4፡16)። ሌሎችን ሰዎች አንፈልግም የምንል ከሆነ ትዕቢተኞች ነን ማለት ነዉ የክርስቶስን ጥበብ መናቅ ነዉ ከማደግ ይልቅ ወደ መንሸራተትና መዉደቅ የሚያመራ ነዉ።

በክርስትና ሕይወታችን ለማደግ የምንከተለዉ ምሳሌ ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ልጆቹ ሰለሆንን ጸጋዉን እየተለማመደ የጌታን መንገድ ይከተላል። ጳዉሎስ ልጁ ለሆነዉ ለጢሞቲዎስ ይህንኑ ሲመክረዉ ነበር። ለጢሞቲዎስ በጻፈዉ መልዕክቱ ላይ የክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ላይ በማበረታታት ይጽፍለት ነበር።

አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታም ከሁሉ አዳነኝ።በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉአንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና(2ጢሞ3፡10-14)

ጢሞቲዎስ መሆን ያለበት ‹‹ይህን እዘዝና አስተምር። በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀውእስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ...ራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና›› (1ጢሞ 4፡12-16) አካሄዱን አያችሁ? ጳዉሎስ ለጢሞቲዎስ ምሳሌዉ ነበር በትምህርቱ ጥራት ላይ ብቻ ሳይሆን በሕይወቱም በተለይም በመከራዉ እግዚአብሔር እንዴት እንዳዳነዉ እና የሕይወቱን ምሳሌነት ትቶለታል። ጢሞቲዎስ በተራዉ ደግሞ ምሳሌ መሆን እንዳለበት ይነግረዋል። በቤተክርስቲያን ዉስጥ አማኞች ለሌሎችን አማኞች እንዲጸልዩ እና ሲጸልዩም ‹‹ ጌታሆይ ይህጸጋ በሕይወቱ ይስራ›› ወይም ‹‹ ጌታ ሆይ በአስቸጋሪ ሁኔታ ሁሉ ዉስጥ በድንቅ ሁኔታ እንደጠበቃት ሁሉ ለእኔም ይሁንልኝ››

የምናድግበት አካባቢ ቤተሰብ መሆን ብቻ ሳይሆን የባዕድ አለምም ነዉ።ዕድገት ፍሬያማ የሚሆነዉ እግዚአብሔር ሲመግበዉ ነዉ። ኢየሱስ እዉነተኛዉ የወይን ግንድ ሲሆኑ በአባቱ የተተከለ ነዉ። እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ፍሬ እንዲያፈራ በአብ ሊጠበቁና ሊተከሉ ይገባል።(ዮሐ 15፡2) መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚሰራዉ እርሱን ለሚወድዱ ሁሉ ለበጎ ነዉ።(ሮሜ 8፡28)።ይህ በጎዉ ነገር ምንድን ነዉ? ይህ በጎ ነገር ምንድን ነዉ? አማኞች ክርስቶስን እንዲመስሉ እንደገና ይሰራሉ ማለት ነዉ።(ሮሜ8፡29) ሁሉም የሕይወት ልምዶች ከሉዑሉ አምላክ ስር ነዉ።የክርስቲያን ሕይወት እድገት ዋናዉ ዓላማ ክርስቶስን መምሰል ነዉ።

እንደሚታወቀዉ ጳዉሎስ ብዙ መከራ፣ችግሮች እና ስደት ገጥሞታል መን ልዩ የሆነ መከራና ችግር የለም።ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት ነዉ እነዚህን ነገሮች ተጠቅሞ ሊያሳድገን የሚችለዉ?

1) **እግዚአብሔር ይፈትነናል። የእርሱን የጸጋዉን ታማኝነት በሕይወታችን ልንለማመድ ያስፈልጋል።ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የገሊላን ባህር እንዲሻገሩ ያዘዘዉን ትዕዛዝ ስለመታዘዛቸዉ አስቡ።(ማር 4፡35-41)። ጥቂት ደቀመዛሙርቱ (ጴጥሮስ፣ እንድርያስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ) ባህሩ ከጀርባቸዉ እንዳለ ያዉቁ ነበርወጀቡም ከፊታቸዉ እንደሚነሳ ያስቡ ነበር ጌታን ታገዘዘዉ በመሄድ ላይ ሳሉ እያለ ራሳቸዉን በወጀብ ዉስጥ አገኙ። *መታዘዝ ወደ አደጋም ሊመራ ይችላል ከዚህ ክፍል የምንማረዉ ቁምነገር መታዘዝ ቀለል ወዳለ ሕይወት ብቻ ሊመራ አይችልም። ወይም ዉድቀት ሲገጥመን ካለመታዘዝ የመጣ ነዉ ማለትም የለብንም በክርስትና ሕይወት የእግዚአብሔር መንገድ ማለት ዉስብስብ ነዉ።***

ጌታ ኢየሱስ ለምንድን ነዉ ደቀመዛሙርቱ በአስቸጋሪ መንገድ እንዲጓዙ የሚፈቅደዉ? ለእነዚህ ሰዎች ደካማ የሆነ እምነታቸዉን ለማሳደግ አስቀድሞ የታቀደ ሊሆን ይችላል።(ማር 4፡40)። ይህ ክፍል የሚያሳየን ኢየሱሰ በአባቱ ላይ ታምኖ እንደተኛ በሁሉም ሁኔታ ዉስጥ በጌታ ላይ መታመን አለብን። በወጀብ ዉስጥ ክብሩን አሳያቸዉ እምታቸዉን አጠነከረ። በኋላም ልክ እንደ ጌታ ስምኦን ጴጥሮስ ነገ ትሞታለህ ተብሎ በአስቸጋሪ ጊዜ በሰላም ተኝቶ ነበር።(ሐዋ12፡1-6)። ያዕቆብ ሲመክረን እንዲህ ይላል፡-

‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት።ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም›› (ያዕ1፡2-4)

መፈተን ለማደግ ወሳኝ ነዉ።

2) **እግዚአብሔር ያነጻናል። በአስራ ሰባተኛዉ ክፍለዘመን የተነሳዉ መጋቢ ዮሐንስ ፍላቭል ሲናገር፡- ‹‹መከራ ነፍሳችንን ያነጻዋል የምናልፍበት ጎዳና ደረቅ ምድረበዳ ቢሆንም ንጹህ የሆነዉ ነፍሳችን አጅግ ከመንጻቱ የተነሳና የለበስነዉ ልብስ ነጭ ነዉ ይህም የሕይወትን ጥራት ያሳያል።**

ጴጥሮስ በመልዕክቱ ዉስጥ ሲያስተምር መከራ ያጠነክረናል ያነጻናልም (1ጴጥ1፡5-6) ከመዝ 119፡6 ላይ የምንማረዉ

እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ፤ አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ።

ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ

አቤቱ፥ ፍርድህ ጽድቅ እንደ ሆነች፥ በእውነትህም እንዳስቸገርኸኝ አወቅሁ። (119: 67,71,75)

በሽታዉ ትልቅ ሲሆን መድሀኒቱም እንዲሁ ትልቅ ይሆናል።በሽታዉ ሐይለኛና አጥፊ ካልሆነ በጸጋዉ ማደግ የሚባል ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር እንደተወህ ሲመስልህና ወይም በመከራዉ ዉስጥ ሲያሳልፍህ ይህን አስታዉስ ‹‹ *እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናልቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።ስለዚህ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ›› (ዕብ 12፡10-12)፤* **ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት የሚመጣዉ ከአን ወይም ከእግዚአብሔር የሚመጣ ዉድ ነገር አይደለም።**

3) **እግዚአብሔር ለአገለግሎቱ ያስታጥቀናል ይህንም የሚያደርገዉ የሚያስፈልገንን ነገር በማዘጋጀት ነዉ። ዮሴፍ በብዙ መከራና ችግር አለፈ ይህንንም ነገር ሲያደርግ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸዉን ነገር በማዘጋጀትና መለኮታዊ የሆነ ግሳጼ ዉስጥ**

አሳለፈዉ ለወንድሞቹም ሲናገር እናንተ ለባርነት ሸጣችሁኝ ነበር ‹‹እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው›› ዘፍ 50፡20

በተመሳሳይ መልኩ ጳዉሎስ በታላቅ መከራ ዉስጥ እያለፈ በመከራ ዉስጥ የሚያልፉትን ያጽናና ነበር ደግሞ በመከራ ዉስጥ እለፉ ያሉትን ሰዎች ያገለግል ነበር፤

የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደ በዛ፥ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና። (2ቆሮ 1፡3-5)

ይህ ለክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ቁሚ የሆነ መመሪያ ነዉ በፊት እንደተማርነዉ በቁሚነት ማደግ እንችላለን፤

ችግሮችን ማሸነፍ

የክርስትና ሕይወት እድገት ግራፉ ቀጥ ያለ አይደለም፤እንደ ልጅ አስተዳደግ አንዳንድ ጊዜ ቅጽበታዊ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሳይታወቀን በቀስታ የሚሆን ነዉ፤ ነገር ግን በምንም ሁኔታ እድገት ከእንቅፋቶች ነጻ አይደለም፤ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያን ሕይወት ከሶስት አቅጣጫ በዉጊያ የተከበበ ሲሆን እነዚህም ከዓለም፣ ከሥጋና ከሰይጣን የሚመጣ ነዉ፤ በዚህ ዉጊያ ሁሉ ለድል የሚያበቁ ሁለት ነገሮችን ማወቅ ያስፈልጋል እነዚህም ጠላትንና ያለህን ነገሮች ማወቅ ነዉ፤

ዓለም የሚባለዉ በዓለም የሚኖሩትንና አለማዊ ሰዎችን ሲሆን እነዚህም እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ናቸዉ(1ዮሐ 2፡16)፤ በክርስቶስ ያለንን እይታና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሊገድል የሚችል ነዉ፤ዴማስን ማየት እንችላለን የጳዉሎስ አጋር የሆነ ሰዉ ነበር(ፊልሞና 24) በአለማዊ ፍቅር ተስቦ ወደቀ (2ጢሞ 4፡10)፤ ምናልባትም ኢየሱስ ከተናገረዉ *‹‹....የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል›› ማቴ 13፡22* ተመሳሳይ ነዉ፤ ጳዉሎስ ዓለምን ስለመጥላት የተናገዉን ነገር መዘንጋት ነዉ (ሮሜ 12፡2፣ ጀ ቢ የፊሊፕስ ትርጉም)

ዓለም ከልባችን ዉስጥ ተነቅሎ ካልወጣ እኛን ሊዉጠን ይችላል። ጥሩ የሆነ የጸጋ ተክል ሲተከል አብሮ አረም ማደጉ አይቀርም። አረምን ወይም ዓለማዊ ነገርን ከልባችን አዉጥቶ የሚገድል ነገር ምንድን ነዉ? ሦስት የማይለያዩ ነገሮችን እናያለን

1) ዓለምን መዉደድ ሰዉ የአብ ፍቅር በዉስጡ የለም(1ዮሐ 2፡15) ሁለቱም ነገር ሊኖርህ አይገባም ከሁለት አንዱን መምረጥ የግድ ነዉ። ትክክለኛዉን ምረጥ
2) አስታዉስ ኢየሱስን የሰቀለችዉ ዓለም ናት የመስቀል ላይ ሞቱ አንተን ነጻ ለማዉጣት ነዉ።(ገላ 6፡14) እንዴት ነዉ አዳኙን ክርስቶስን ለመግደል ከሚመክሩ ጋር የምትስማማዉ?
3) ዓለም የሚለዉ በዚህ ሀሳብ ሲተነተን አጭር ሕይወትን የሚያሳይ ነዉ(1ዮሐ2፡17) በሰማይ ሀብትን ለማከማቸት ራስን መስጠት ያስፈልጋል።(ማቴ 6፡19-21) ከዮሐንስ ኪዉተን ልምምድ የምንማረዉ መንፈስ ቅዱስ በልብህ በሙላት እንዲፈስና እንዲቆጣጠርህ መፍቀድ ያስፈልጋል በዚህ ጊዜ ዓለም አቅመቢስ እና ለእድገትህ እንቅፋት በሚሆንብህ ጉዳይ ድልን ትጎናጸፋለህ።

ሥጋ የሚለዉ በአዲስ ኪዳን ዉስጥ አንዳንድ ጊዜ ‹‹ስጋ፣ደምና አጥንት›› ተብሎ ተቆጥሯል። በጳዉሎስ መልዕክቶቹ ሁሉ ዉስጥ ስለ አሮጌዉና ስለወደቀዉ የሐጢአተኛዉ ተፈጥሮ ነዉ። ክርስቲያኖች እንደ ስጋ ፈቃድ የሚኖሩ አይደለም በዚህ የሐጢአተኛዉ ተፈጥሮ ቁጥጥር ስር አይደሉም ሆኖም ከዚህ የሐጢአተኛ ተፈጥሮ ተጽእኖ ነጻ አይደሉም። አንድ ጀርመናዊ ቅዱስ ይህን ብሎ ነበር ‹‹ እኛ የምንቃጠል እቃዎች ስንሆን እሳቱን ማስወገድ አለብን›› ክርስቲያኖች አዳማዊ ባህርይ እንዲያድግ የሚያደርገዉን ሀጢአተኛ ባህርይ ነዳጅ እስካላስወግድን ድረስ በጸጋዉ ልናድግ አንችልም።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳናድግ እንቅፋት ከሚሆነዉ አሮጌ ባህርይ ላይ እንዴት ድልን ልንቀዳጅ እንችላለን? ጳዉሎስ እንደገና በቆላስያስ መጽሐፍ ዉስጥ በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርጎ ይጽፋል (ቆላስስ 3፡1-17) ዋና ነጥቡም፡-

1) አሮጌዉ ባህርይ በዉስጥህ በቋሚነት እንደሚገኝ እወቅ።ጳዉሎስ በቆላ3፡5-9 ዉስጥ *‹‹እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው...››* እነዚህ ነገሮች በአዉነተኛ ክርስቲያን ሕይወት ዉስጥ ሊኖሩ የሚችሉ መቅሰፍቶች ናቸዉ።

2) በአንተ ዉስጥ የሚያድረዉ ሐጢአት በአንተ እይታ ያለ ሳይሆን በፈራጁ እግዚአብሔር እይታ የሚታይ ነዉ ሀጢአት የእርሱን ቁጣ ያመጣል (ቁ.6)

3) እንደ ክርስቲያን ማን እንደሆንክ አስብ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለሃል፣ተቀብረሃል ከሞትም ተነስተሃል (ቆላ 3፡1-3) ከዚህ በኋላ በሀጢአት ስር አይደላችሁም(ሮሜ6፡14-18) አሳባችሁን በክርስቶስ ላይ እና በሕይወታችሁ ላይ አትኩሩ በክርስቶስ ባገኘሁ አዲስ ሕይወት ቅድስና ላይ ትኩረት አድርግ (ቆላ 3፡1-4፣9-10)

4) ሐጢአትን ተቃወም፤አታመቻምች ግደለዉ እንጂ (ቆላ3፡5)

5) ክርስቶስን በሚመስል ሕይወት ባህርይ ይቀየር፤‹‹...የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ፤›› ቆላ3፡12፤ በዚህ ሁኔታ ለአሮጌዉ ባህርይ የምትሰጡት ቦታ አናሳ ይሆናል፤(ቁ.12-17)

በግቢህ ዉስጥ የሚተከለዉ አትክልት ወይም አበባ በየቀኑ እንክብካቤ የሚፈልግ ነዉ፤ አረም በተፈጥሮ ስለሚበቅል ማስወገድ ያስፈልጋል፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ፍሬን ለማፍራትና ወደ ብስለት ለማደግ አረሞችን ማስወገድና እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል፤

ጴጥሮስ ሲናገር ዲያቢሎስ የሚዉጠዉን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችን ይዞራልና ይህ ክርስቲያኖችን ለመዋጥና ለማጥፋት ነዉ፤ እኛን ከክርስቶስ አይነጥለንም ነገርግን በዙሪያችን የሚዞረዉ በንዴት ነዉ(1ጴጥ5፡9)፤እድገታችን ላይ እንቅፋት ለመፍጠርና ሊያታልለን ነዉ፤ ከክርስቶስ ለመነጠል ብዙ ስራዎችን ይሰራል ጥሩ ያልሆነ ሐሳቦችን ወደ አሳባችን በማስገባት ልክ በኤደን ገነት ሔዋንን እንዳታለለዉ አይነት ማለት ነዉ፤‹‹*ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት (ዘፍ3፡1)*፤ በርግጥ እግዚአብሔር ለሔዋን በገነት ዉስጥ ካለዉ ፍሬ ሁሉ እንድትበላ ነጻነት የሰጠ ሲሆን አንደኛዉን ግን እንዳትበላ አዘዞ ነበር(ምን አይነት እገዚአብሔር ነዉ ብላ እንድትጠራጠር አደረገ ሰይጣን አታለላት እርሷም አመነች፤(ዘፍ3፡13)

ሰይጣንን አንዴት እንቋቋመዋለን? የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ በማንሳት ነዉ፤የጸጋዉን ወንጌል ቃሉን ጽድቁን (ኤፌ6፡10-20) ልክ ኢየሱን ለመፈተን ሲመጣ ኢየሱስ እንደተቋቋመዉ እኛም መቋቋም አለብን በክፉ ቀን መቋቋም የምንችልበትን ዕቃ ማንሳት (ማቴ 4፡4፣7፣10)ትልቁ

መከላከያችን ልባችንን በእግዚአብሔር ፍቅር መጠበቅ ነዉ (ይሁዳ 21) ቃሉን በማመን እና በመታዘዝ የእርሱን የጦር መሳሪያ በመልበስ ጭምር ማለት ነዉ ኢየሱስም በስኬት አሸንፎታል።

ጳዉሎስ እንደሚናገረዉ ክርስቲያኖች የሚቆሙበት ብዙ ነገሮች አሉ ሁልጊዜ በሁሉ ነገር መቆም። ይህ የዉጊያ ትኩሳት ሲሆን ወደ እድገትና ብስለት የሚወስደን ስለሆነ መቆም ያስፈልጋል።ብዙ እናቶችን በመጀመሪያ ልጅ ሲወልዱ ምን እንደሚሆን ጠይቁአቸዉ የእድገት ምልክት የሚያሳዩ ምንድን ናቸዉ? ፈተና ወደ ትልቅ ስፍራ ያመጣናል። አንዱ የእድገት ምልክት መረጋጋት ነዉ። ይህም በመንፈሳዊ ዓለም ዉስጥ ወደ አዲስ ደረጃ ላይ የሚያደርስ ነዉ። መከራንና እንቅፋቶችን ለመቋቋም መቆም እና መንፈሳዊ እድገት ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድንና ማሸነፍ ይገባል።

በአዲስ ኪዳን ዘመን በሚያሳዝን መልኩ ከፍተኛ የሆነ መከራና ስቃይ ሲገጥማቸዉ ጥቂት ክርስቲያኖች በተለይ በመንፈሳዊ ነገር ልጅ የሆኑ ወደ ብስለት ደረጃ የደረሱ አሉ(1ቆሮ 3፡1-2፣ ዕብ 5፡11-14)

ልጆች ደስ ይላሉ ወላጆችንም ያስደስታሉ ነገር ግን ልብ የሚሰብረዉ በአአምሮም በስጋም ማደግ ሲያቅታቸዉ ነዉ በተለይም የበሽታና ሕመም ስሜት ካላቸዉ ያሳዝናል። በዚህ ክፍል ማየት ያለብን እንደ ክርስቲያን መቆም ያልቻልነዉ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ አለመቻላችን ነዉ አለማደግ የበሽታ መኖር ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ምክር ይሰጠናል *‹‹ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ...›› (ዕብ 6፡1-3)*

መንፈሳዊ ምርመራ

በክርስትና እያደግህ የምትሄድ ጤነኛ ነህን? ሕመም ተሰምቶህ ወደ ሐኪም ቤት ስትሄድ ሐኪሙ ለምርመራ የተለያየ ነገር ያደርጋል፣ የደም ብዛትህን ይለካል፣ዓይን፣ጆሮ፣ ደምና ሰገራ እንድትሰጥ ትደረጋለህ። ስለመንፈሳዊ ምርመራ የሚቀጥሉት ገጾች መንፈሳዊ ጤንነትህን እንድትመረመር የሚረዳህ ስለሆነ መንፈሳዊ ሕይወትህ በምን አይነት ሁኔታ እንዳለ ለመመርመር የሚረዳህ ነዉ።

1) መንፈሳዊ ግብ። የክርስቲያን የዕድገቱ ግብ ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ እና እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል የወሰነ መሆኑን ተረድቻለሁን? ይህ ግቤ ነዉን?

2) **የምግብ አቅርቦት፤ጤነኛ የሆነዉን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እየተመገብኩ ነዉን? የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን እሰማለሁን? የሰማሁትንስ እታዘዛለሁን? በግሌ ለማጥናትስ ፍላጎቱ አለኝን? ለስጋዊ ሰዉነቱ ምግብ በየጊዜዉ እንደምመገብ እንዲሁ ለመንፈሳዊ ዕድገቴስ ምን ያህል በየጊዜዉ መንፈሳዊ ምግብ እየተመገብሁ ነዉ?**

3) **ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣዉ ቃል መኖር፤ መጽሐፍ ቅዱስን በመደበኛነት አጠናለሁን? ሳጠናስ እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱ በማመን እና በመቀበል ነዉን? (2ጢሞ3፡16-17) እንደ እግዚአብሔር ቃል መቀበል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ዓላማዉ ምንድን ነዉ? እንዲህ ብየስ እጠይቃለሁ?**

ሀ) **ማስተማር፤ የትኛዉ መጽሐፍ፣ቁጥርና ምዕራፍ ነዉ (ስለ እግዚአብሔርና ባህርዩ፣ ሰዉና ሐጢአት፣ክርስቶስና ስራዉ፣የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት፣ ክርስቲያናዊ ሕይወት፣የእግዚአብሔር ዓላማ፣የቤተክርስቲያን ሕብረት፣ዓለም የምትፈልገዉ?**

ለ) **መገሰጽ፤ እግዚአብሔር በሕይወቴ ያሳየኝ ሐጢአት አለ? ልናዘዘዉና ንስሀ መግባት ያለብኝ ሐጢአት አለ?**

ሐ) **ማረም፤ የማነበዉ ክፍል እንዴት ነዉ እግዚአብሔር በሚፈልገዉ መንገድ መሆን የምችለዉ?**

መ) **መሰልጠን፤-ስለ ሐላፊነቴ ምንድነዉ የተማርኩት? እግዚአብሔረ የሰጠኝን ሀብ እንዴት ነዉ የምጠቀመዉ?**

ሠ) **መለማመድ፤እግዚአብሔርን በማምለክ እየጨመርኩ ነዉ? ደስታዬን በግሌና በአደባባይ በማመስገን በመጨመር ላይ ነኝን?**

ረ) **አገልግሎት፤ ክርስቶስ የሰጠኝን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለሌሎቸ በረከት እንዲሆን ተጠቅሜበታለሁን? እንዴትና መቼ ልጠቀምባቸዉ እንደምችል በዉል ተረድቼአለሁ? ሌሎችን በደንብ ለማገልገል አበረታታለሁን? ወይስ ራሴን ለማሳደግና ከሌሎቸ የተሻልኩ ነኝ ብዬ አስባለሁ? ስጦታዎቼን፣ሀብቴንና ገንዘቤን ለእርሱ አገልግሎት አዉላለሁን?**

ሰ) **ምስክርነት፤ሕይወቴ ለዓለም ብርሃን ሆኖ ያበራልን? ሕይወቴ ለቤቴ አና ለቤተሰቤ ጨዉ ሆኖአልን?የት ነዉ የምሰራዉና የማጠናዉ?የት ነዉ የምኖረዉ የምጫወተዉስ? ባገኘሁት አጋጣሚ ስለ ክርስቶስ እመሰክራለሁ? እጸልያለሁ?**

ሸ) **ሕብረት፤ራሴን ለቤተክርስቲያን እሰጣለሁ? ስለ ራሴና በዙሪያየ ላሉ ክርስቲያኖች እጠነቀቃለሁን? ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች የእግዚአብሔርን ጸጋ እጠይቃለሁን? በትዕቢት ተይዣለሁ? ወይም ቁጭ ብዬ ፍላጎቶቼን ምን እንደሆኑ አዉቄያለሁን?**

ክርስቲያን ወዳጆቼ ከእኔ የተሻሉ እንደሆኑ አስባለሁን? ለማገልገል ዝግጁ ነኝ? የሌሎችን ሰዎች ስጦታ ስመለከት አደንቃለሁን? ስለስጦታቸውም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁን? ከስኬቴ የተነሳ ጥቂት የሆኑ ክርስቲያኖች ወደ ሕይወቴ እንዲመጡ እፈቅዳለሁ ወይስ ለእግዚአብሔር በረከት መሳሪያ ሆኛለሁ?

ቀ) *አቅርቦት፤* ችግሮችና መከራዎች ሲገጥሙህ እንዴት ነዉ የምትጋፈጣቸዉ? የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም አብረህ የምትሰራ ሰዉ ነህ? ያደኩት አስተዳደግ በክርስቶስ ላይ እንድታመንና የእርሱን አላማ በማወቅ መለወጥና መባረክ ነዉን? በራሴ አልተማመንም? ባለፍኩት የጨለማ ዘመን የተማርኩት ነገር አለ? ነዉ ወይስ ከጨለማዉና ችግሩ ማረፌ ብቻ ነዉ?

በ) *ባህርይን ማሻሻል፤* በእግዚአበሔር ጸጋ ንጹህና ጨዋ ሰዉ ነኝን?ኢየሱስ እኔን የተባረከ ሰዉ ብሎ ይገልጸኛል?(ማቴ5፡1-12)

ተ. *መታዘዝ፤* የጌታን ትዕዛዛት እወዳቸዋለሁን? በሕይወቴ ላይ የሚገጥመኝን የእግዚአበሔረነ ስራ የሚቃወመዉን እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ለመቃወም የተረጋጋ ሕይወት አለኝን?

ብዙ ቁሳቁስ ከሌለኝ ከዝሙት፣ራስን ያለልክ ከመዉደድ፣ከስግብግብነት ሕይወት ነጻ ነኝን? በገንዘቤ እና ንብረቴ ላይ እኔ ጌታ ሆኜ እቆጣጠረዋለሁ ወይስ ገንዘቡ ነዉ እኔን የሚቆጣጠረኝ?

ቸ. *የሐጢአት ባህርይ፤* በሕይወቴ ዉስጥ ላለ ሐጢአት የሞትኩ ነኝን? የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ለመልበስ ፍላጎቱ አለኝ?

ነ. *መንፈሳዊ ዉጊያ፤* በእርሱ ሳልያዝ የሰይጣን ስራ እንዳለ አምናለሁ? በሕይወቴ ሊያደርግ ያለዉን ስልት በማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም ዉጊያዉን ለመቋቋም ዝግጁ ነኝን? ከእርሱ ዉጊያ የተጠበቅሁ ነኝን?

ኘ. *ክርሰቲያናዊ ዕድገት፤* እንደ ክርስቲያን እያደግሁ ነኝን? ሕብረት በማድረግ እያደግሁ ነኝን? በቤተሰብ ሕይወትስ እያደግሁ ነኝን? በየቀኑ ባለኝ እንቅስቃሴስ? በግል ሕይወትስ?

የመጻሕፍት ዝርዝር

የሚከተሉተ መጻሕፍቶች የተዘጋጁት ከመሰረታዊ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ቤተመጻሕፍት ሲሆን ከአሳታሚ ድርጅቱ ነዉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ጀ.ግሪሻም ማቸን፤ ግልጽና ሊነበብ ከሚችል አዲስ ኪዳን ከአዲሰ ኪዳን መጽሐፍ ነዉ። እንዲበብ የሚመከር ነዉ።

ጂኦፍሪ ቶማስ፤ *መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፤* መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት በግልህ ማጥናት እንዳለብን ጥበባዊ የሆነ ምክርን ይሰጣል።መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት መርሀ ግብርንም ይጨምራል።

ጂኦፍሪ ዊልሰን፤ ሲሪየስ የአዲሰ ኪዳን ማብራሪያ (ፔፐር ባክ ማብራሪያ በጳዉሎስ መልዕክቶች)

የክርስቲያን አስተምህሮ

ኤል በርኮፍ፤ *የክርስቲያን አስተምህሮ ማጠቃለያ፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ዋና ዋና የክርስቲያን አስተምህሮ።

ሲ. ብራወን፤ *መለኮታዊ የክርስቶስ ክብር፤* ጥናተ- ክርስቶስ አካል።

ደብሊዉ ጄ ግሬየር።ጠቃሚዉ ከስተት፤ ስለ ወደፊቱ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ።

አር ቢ. ኩይፐር፤ *መለኮታዊ የክርስቶስ ክብር፤* ሊነበብ የሚችል በቤተክርስቲያን ተፈጥሮ ላይ

ዲኤም ሊዮይድ ጆንስ፤ *ሥልጣን*፤ በመጽሐፍ ቅዱስ *ሥልጣን* ላይ ጥናት እና የመንፈስ ቅዱሰ ሥራ ብዙ ክርስቲያኖችን ጠቅሟል።

ጆን ሙራይ፣ መቤዠት፤ የሚፈጸምና የሚተገበር፤ በክርስቶስ ስራ ላይ የሚተገበር

ጆጂ ማቼን፤ ስለ ሰዉ የክርስቲያን አመለካከት፤ በ20ኛ ክፍለዘመን ላይ የተነሱ ሊህቃንና የክርስቲያን መሪዎች፤